# ስለ‘‘ታቦተ ጽዮን’’
# እና
# ‘‘ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ’’
# ማለትም፡
# ‘‘ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል ነሣ’’
# ስለተባለው መለኮታዊ ቃል፤

+++

ይኸውም፡ በሙሴ አማካይነት፡
ለሕዝበ እስራኤል፡ በቃል ኪዳን የተሰጠችው፥
በንግሥተ አዜብ
እና
"የንጉሥ ወንድ ልጅ" የሚል ትርጉም ባለው፥
በሕዝባዊው አጠራርም፡ "ምኒልክ" በተባለው፡
በልጇ በቀዳማዊ እብነ-መለክ ልኡክነት፡
ወደኢትዮጵያ የመጣችው ታቦተ ጽዮን፥
ለ፫ሺ ዓመት ከቆየችበት፡ ከቅድስት አኵስም ጽዮንና
በቅዱሳን ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና
በቅዱሳት ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ጠባቂዎቿ እጅ፡
የዛሬ ፪ሺ ዓመት ገደማ፡
በሰውነት፡
ወደኢየሩሳሌም በክብር ተመልሳ፡
ወደቤተ መቅደሷ መግባቷን የሚያዘክር፡
መንፈስ ቅዱስ የከሠተው፡ ሃይማኖታዊ መልእክት።

+++

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ በኤፌሶን ለሚገኙ፡ ከጣዖትና ከባዕድ አምልኮ፡ ወደአዲሱ የክርስትና ሃይማኖት ለገቡ፡ ምእመናን ምእመናት፡ በጻፈላቸው መልእክት፡-

"አሐዱ እግዚአብሔር፤ ወአሐቲ ሃይማኖት፤ ወአሐቲ ጥምቀት"

ማለትም፡ "አንድ እግዚአብሔር፤ አንዲት ሃይማኖት፤ አንዲት ጥምቀት።"፥ ወይም፡

"እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሃይማኖትም አንዲት ናት፤ ጥምቀትም አንዲት ናት።" ማለቱ፡

በመጀመሪያው ዘመን አበው ወእማት፡ አዳምና ሔዋን፥ ኖኅና ሓይከል፥ መልከ-ጼዴቅና ሳሌም፥ አብርሃምና ሣራ፥

በመካከለኛው ዘመን ሕግና ነቢያት ደግሞ፡ ሙሴና ሲጳራ፥ ዳዊትና ቤትሳባ፥

በመጨረሻው ዘመን ምሕረትና ዘመነ መንፈስ ቅዱስም፡ በንጽሕተ ንጹሓን፥ በቅድስተ ቅዱሳን፥ በብፅዕተ ብፁዓን፥ በቡርክተ ቡሩካን፥ በአንቀጸ ብርሃን ድንግል ማርያም ክበበ ትስብእት (ውሱን ሰውነት)፡ ለዓለሙ፡ በገሃድ የተገለጸውና የታየው፡ እውነተኛው አምላክ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ <u>ያው እርሱ ራሱ፥ ቀዳማዊው (የቀደመው)፥ በአካሉና በባሕርዩም፡ ያው አንዱ መኾኑን፡</u> አስተማምነው እንዲቀበሉ፡ ለማድረግ መኾኑ አያጠራጥርም። (ኤፌ. ፬፥ ፫።)

እንዲሁም፡ የእነዚህ፡ ታላላቅ፡ አባቶችና እናቶች፥ ነቢያንና ነቢያት፥ ሐዋርያንና ሐዋርያት ሃይማኖት፥ ወይም፡ እምነት፡ <u>አንድ ከመኾኑ ጋር</u>፥ ገና፡ በዘመነ ክርስትና፡ በውኃ ሳይጠመቁና ሳይወለዱ፥ ሥርዓቱም ሳያስፈልጋቸው፡ <u>የእግዚአብሔር ልጅነትን አግኝተው፡ በሕያውነት የቀጠሉ መኾናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።</u>

ይህ እውነታ፡ እርሱ እግዚአብሔርና የእርሱ የኾነው ኹሉ፡ በህልውናው (በአነዋወሩ) ረገድ፡ አንድ እንደኾነ፥ በዚህ ምንነቱና ማንነቱም፡ በሕያውነት፡ ለዘለዓለም የሚቀጥል መኾኑን፡ ሃይማኖተ ቢስና ተጠራጣሪ ለኾነ ሰብኣዊ እምሮ (አእምሮ)፡ በአጥጋቢ መልኩ፡ የማያወላውል ምላሽን ይሰጣል።

ይህን፡ ከላይ የታተተውን እውነታ፡ መነሻና መሠረት በማድረግ፡ ታቦተ ጽዮን፡ "ነያ ዝየ! ወነያ ከሓክ!" ማለትም "እዚህ ናት! ወይም፡ እዚያ ናት!" በማትባለው፡ በሰማያትና በምድር ዓለማት፡ በምልዓት ሰፍና ባለችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በህልውናዋ (በአነዋወርዋ) ረገድ፡ <u>**አንዲት** መኾኗን</u>፡ በርግጠኝነት መቀበል ይቻላል፤ ያስፈልጋልም።

አዎን! ለባለራእዩ፡ ለዮሓንስ፡ በሰማያት፡ የተገለጸችውና የታየችው፡ የኪዳኗ ታቦት፡-

- በመካከለኛው፡ ዘመነ ሕግና ነቢያት፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ሕዝብ ቀድማ የተሰጠችው፥

- ኋላም፡ በንግሥተ አዜብና በልጇ በቀዳማዊ እብነ መለክ (ምኒልክ) ልኡክነት፡ ወደኢትዮጵያ የመጣችው፥

- ከ፩ሺ ዓመት ቆይታም በኋላ፡ ከቅድስት አኵስም ጽዮን ተነሥታ፡ በኢትዮጵያዊት እናቷ፡ በቅድስት ሓና ማሕፀን ውስጥ፡ በክብርና በመላእክት ጥበቃ ተከልላ፡ ወደኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሷ የተመለሰችው፥

- በመጨረሻም፡ በምድር ላይ የቆየችበትን፡ የቤዛነትና የድኅነት መለኮታዊ ዓላማ፡ በድል ፈጽማና አጠናቅቃ፡ ወደሰማያት ያረገችው፡ <u>በአካልዋና በባሕርይዋ፡ ያው፡ **አንዲት** ናት።</u>

# ታቦተ ጽዮን፡
# ማረፊያዋና ማደሪያዋ አድርጋት ከቆየችባት ከአኵስም፡ ወደኢየሩሳሌም፡ በክብር የተመለሰችው፡ እንዴት ነው? መቼስ ነው?

ለዚህ መልስ የሚኾኑትን፡ የመንፈስ ቅዱስን እውነትና እውቀት ለማግኘት፡ ከዚህ የሚከተሉትን እውን ኹኔታዎች፡ በብርቱ ሃይማኖታዊ ልቦና መረዳትና መገንዘብ፥ ማስተዋልና ማመንም ያስፈልጋል። እነዚህም፡ እንዲህ በሚሉ ሓተታዎች፡ እነሆ ተገልጸው ቀርበዋል፡-

በመጀመሪያ ነገር፡ ራሳቸውን፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት አይሁድ፡ "በአባትነትና በእናትነት ፍቅር፡ እጅግ በሚወድዳቸውና በሚንሰፈሰፍላቸው፥ ለእነርሱም ሲል፡ ማንኛውንም ዓይነት መሥዋትነት ከመክፈል፡ ወደኋላ በማይለውና በማያመነታው፡ በአምላካቸው በእግዚአብሔር ላይ፡ ምን ዓይነት ድርጊትን ፈጸሙ?" ለሚለው መጠይቃዊ ትች፡ በቅድሚያ፡ ተገቢ መልስን መስጠት ያስፈልጋል።

መልሱም፡ ባጭሩ፡ እኒሁ፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት አይሁድ፡ "በአባቶቻችን፡ በአብርሃም፥ በይስሓቅና በያዕቆብ ቃል ኪዳን፡ አምላካችን ነው!" የሚሉትን እግዚአብሔርን፡ በከሃዲነታቸውና በዓመፀኛነታቸው፥ በምንዝርናቸውና በባዕድ አምልኮ ባህላቸው፡ አስቀኑት!" ነው።

"ታዲያ! በዚህ ጊዜ፡ እርሱ፡ የኢትዮጵያ አምላክ፡ ለእነዚህ ተፃራሪዎቹ፡ ምን ዓይነት ወሮታን መለሰላቸው?" የሚል ተከታይ ጥያቄ ይኖር ይኾናልና፡ መልሱን፡ እንዲህ በሚል ቃል አጠቃልሎ መስጠት ይቻላል፦

እንደስሙ፡ ትሑትና ቅን፥ የዋህና ገር የኾነውን፡ ሙሴን፡ እግዚአብሔር፡ ከግብፅ ወደኢትዮጵያ አምጥቶና ከኢትዮጵያዊው ካህን ንጉሥ፡ ከዮቶር፡ ስለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት አሳውቆ፡ እርሱ ሙሴም፡ ይህንኑ እምነት ከተቀበለና ኢትዮጵያዊቷን፡ የዮቶርን ሴት ልጅ፡ ሲጳራን አግብቶ ልጆችን ከወለደ በኋላ፡ እርሱን፡ ሙሴን፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ፡ ወደግብፅ ልኮ፡ በእርሱ አማካይነት፡ እነርሱ፡ ይማቅቁበት ከነበረው፡ የባርነት አገዛዝ፡ በታላቅ መለኮታዊ ኃይሉ፡ ነጻ አወጣቸው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ ኹሉ የሚበልጠውን፡ ልዩ ቸርነትም አደረገላቸው፤ ይኸውም፡ በመጨረሻ፡ የቅርብ ባለሟሉና አገልጋዩ ከኾነው፡ ከሙሴ ጋር፡ ቃል ኪዳን ተካይዶና ተዋውሎ፡ ታቦተ ጽዮንን ሰጣቸው። እርሱ፡ የኢትዮጵያና የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፡ በሙሴ አማላጅነት፥ በዚች፡ በታቦተ ጽዮን ጣዖታዊ ምሳሌነትም፡ ራሱን፡ ለእነርሱ፡ ቤዛ አድርጎና አሳልፎ ባይሰጣቸው ኖሮ፡ ከመካከላቸው፡ አንድም ዘር የሚተርፍ ሳይኖር፡ ኹሉም፡ ከገጸ ምድር ተደምስሰው በጠፉ ነበር።

ለዚህ ታላቅ በደላቸውና ኃጢአታቸው ማስተስረያ እንዲኾን በሚል፡ አዎን! ከእዚህ በፊት፡ ሰዎችም ኾኑ፡ መላእክት፥ ባጠቃላይ ፍጥረታት፡ ዐልመው፥ ተመኝተውና ጠይቀው የማያውቁት፡ አንዳች፡ ልዩና ብርቅ፥ ዕፁብና ድንቅ የኾነ ነገር፡ በምድር ላይ ተከሠተ፤ ታየ።

ያም፡ በምድር ላይ የተከሠተው፡ ልዩና ብርቅ፥ ዕፁብና ድንቅ የኾነው ነገር፡ ምንድር ነው? ትሉ እንደኾነ፡ መልሱ፡ አኹንም፡ እጥር ምጥን ያለ፡ እንዲህ የሚል ነው፦ በህልዎት (በአነዋወር) አካሉና ባሕርዩ፡ **"እውነት እና መንፈስ"** በመኾኑ ምክንያት፥ በዚያው፡ በ**"እውነተኛነት እና በተቀደሰው መንፈስ"** መመለክ የሚፈልገው እግዚአብሔር፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" የሚሉትን፥ እርሱ የሚወዳቸውን፥ እነርሱ ግን፡ የሚጠሉትን፡ እስራኤላውያንን፡ ከመጥፋትና ከመደምሰስ ለማዳንና ለመታደግ፥ ብሎም፡ የባዕድ አምልኮ ጥማታቸውን ለማርካት ሲል፡ ራሱ ፍቅር የኾነው እግዚአብሔር፡ በፍጹም ትሕትና፡ እንደፍጡሩ፡ በጽላት (ደንጊያዎች) ላይ ተቀርጾ፡ <u>**ጣዖት** መኾኑ ነዋ!</u>

**"ምን ይረቅ! ምን ይደንቅ! ለዚህ አንክሮ እና ተዘክሮ ይገባል።" ሊባልለት የሚገባው፡ ይህ አምላካዊ ቸርነት፡ በተግባር ተፈጽሞ፡** እውን የኾነው፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በክበበ ትስብእት ተገልጾ፡ ከሰይጣንና እኵያን ኃይላት ጋር፡ በፍቅር ተዋግቶ፡ በዕፀ መስቀል ላይ፡ ደሙን በማፍሰስና ሥጋውን በመቆራረስ፡ ለዓለሙ፡ ሰላምን ከማስገኘቱ አስቀድሞ መኾኑ ሊጤን ይገባል።

ቀጣይ በኾነው፡ በማካተቻው ነገር ደግሞ፡ አዎን! ይህ፡ ወደር የማይገኝለትና አማልክት የማይወዳደሩት፡ የእግዚአብሔር መሥዋዕትነት፡ ምንን እንደሚመስል፡ እስኪ፡ ለአንድ አፍታ እንመልከተው!

"አንዲት እናት"፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩትን፡ የእርሱን ልጆች፡ በተጠሪነት፡ አንከባክባ ለማሳደግ፡ በቅድሚያ፡ ብትችል፡ በሞያዋ ሠርታ፥ ቀጥሎ፡ ምናልባት፡ ባትችልና ሞያ ባይኖራት፡ በወዟና በላቧ፡ ጉልበቷን ሠውታና ደሟን አንጠፍጥፋ፥ በማብቂያው ግን፡ ይህ ኹሉ አማራጭ ካልተገኘና ምንም ዓይነት መፈናፈኛ ቀዳዳ ከሌለ ደግሞ፡ ሥጋዋንና ክብርዋን፡ ለገንዘብ በመሸጥ፡ <u>ጋለሞታ፥ ወይም፡ ሴትኛ አዳሪ</u> በመኾንና በመባል፡ ልጆቿን፡ ከመብል ረሃብና ከውኃ ጥም የምትታደግ፡ <u>እውነተኛ ሞግዚት</u>ን ይመስላል። (ዮሐ ፫፥ ፲፮።)

አዎን! እግዚአብሔር፡- "ዐረግከ ውስተ አርያም፡ ጼዊወከ ጼዋ፥ ወወሀብከ ጸጋከ፡ ለዕጓለ እመሕያው!" ይኸውም፡

"ኮነት መንግሥተ ዓለም፡ ለእግዚአብሔር ወለመሲሑ፤ ወይነግሥ ለዓለመ ዓለም።" ማለትም፡

"የዓለም መንግሥት፡ ለእግዚአብሔር እና ለመሢሕ ልጁ ኾነች፤ በእርሷም፡ ለዘለዓለም ይነግሣል!" ተብሎ የተነገረልህ፡ አንተ፡ መሲሕ ኢየሱስ'፡

"ምርኮህን ማርከህ፥ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋህንም፡ ለማርያም ልጆች ሰጥተህ፡ ወደሰማይ ዐረግህ።" ይህም፡ በበለጠ ሲብራራ፡

"ሰዎች፡ በተፈጥሮ ያገኙትን፡ እግዚአብሔራዊ ማንነታቸውን፡ በፍላጎታቸውና በምርጫቸው፡ ወደሰይጣንነት ለውጠውና እየራሳቸውን፡ ለዲያብሎስ አገዛዝ አስማርከው፡ ያስወሰዱትን ነፍሳቸውን ከማረከህ በኋላ፡ በድል አድራጊነት፡ በሓዋርያትና በመላእክት አጀብ ኾነህ፡ ወደጽርሓ አርያም መንበረ መንግሥትህ ዐረግህ፤ በእውነተኞቹም፡ የማርያም ልጆች ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስህ ተመልሰህ፡ ዐደርህባቸው።" በሚለው ቃሉ፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ ያደረገው ተከታታይ ቸርነቱ፡ ሲገለጥ ኖርዋል። (መዝ. ፷፯፥ ፲፰፥ ራእ. ፲፩፥ ፲፭።)

እርሱ የሚቀበለውን የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኮውን፡ እንዲህ፡ ወደመሠረታዊው እና ወደጥንታዊው መንፈሳዊ ልኅቀቱና ማዕርጉ፥ ክብሩና ደረጃው፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሸጋግሮ፡ ወደነበረበት ከመመለሱ በፊት፡ እግዚአብሔር፡ ለሚወዳቸው፥ እነርሱ ግን፡ ለሚጠሉት ፍጡራኑ አይሁድ፡ ከከፈላቸው፡ ሥፍር ቍጥር ከሌላቸው፡ ከታላላቁ፡ የመሥዋዕትነት ቸርነቶቹ መካከል፡ አንዱና ዋነኛው፡ ይህ፡ በጽላተ ሙሴ አማካይነት፡ ጣዖትን መስሎ የመቅረቡ ዝክረ ነገር መኾኑን፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው የእውቀት ኃይል በመጠቀም፡ እውነታውን መረዳት፡ ለማንም ሰብአዊ ፍጡር ሳይቀር የሚያስፈልገው ይኾናል።

እንዲህ ከኾነ፡ በእግዚአብሔር አብ ጣቶች፡ እግዚአብሔር እም በኾነችው፡ በጽላቱ ላይ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር (ጸሓፊነት) የተቀረጹት፡ ፲ቱ (ዐሠርቱ)፡ የእግዚአብሔር ቃላት፡ <u>እርሱ ራሱ፡ ትሑቱና ገሩ **እግዚአብሔር ወልድ** መኾኑን፡ አስተማምኖ ማወቅና መቀበል ይቻላል፤ ይገባልም።</u>

እራሱ፡ እግዚአብሔር የኾነውና በጽላቱ ላይ ያደረው፡ "ይህ ቃል ነው!" በመዝሙረኛውና በባለቅኔው ብዕር፡-

"እስመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤ ወአብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤ ዛቲ ይዕቲ ምዕራፍየ ለዓለም።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤ ማደሪያውም፡ ትኾነው ዘንድ፡ ወዷታል፤ 'ይህች፡ ለዘለዓለም ማረፊዬ ናት!' አለ።" ከተባለችውና ለቃሉ፡ ጊዜያዊ ማረፊያ ከኾነችው፡ ከአኵስም ጽዮን ተነሥቶ፡ ወደዘለዓለማዊና ሕያው ማረፊያው፡ አማናዊቷ አኵስም ጽዮንና ጽላተ ኪዳን ዘሙሴ በኾነችው፡ በድንግል ማርያም ማኅፀን ውስጥ፡ ሰው ኾኖ **የተቀረጸው! የተሣለው!** አዎን! እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር የኾነውና በጽላቱ ላይ ያደረው፡ "ይህ ቃል ነው!" (መዝ. ፻፴፩፥ ፲፫-፲፬። ዮሓ. ፩፥ ፲፬።)

እንግዴህ፡ ይህች፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ሕዝብ ተሰጥታና ወደአኵስም መጥታ፡ በኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና በኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ስትጠበቅ የቆየችው፡ ታቦተ ጽዮን ናት፡ እንዲህ፡ **"በድንግል ማርያም ክበበ ትስብእት፡ ሰው ኾና"**፡ ተመልሳ፡ ወደኢየሩሳሌም ቤተ-ምኵራብ የገባችው።

አዎን! ድንግል ማርያም፡ አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን ለመኾኗ፡ በአይሁድ ዘንድ፡ ስንኳ ሊደረግ ቀርቶ፡ ሊታሰብ እንኳን የማይቻል ኾኖ ሣለ፡ እንዲህ፡ **በሴትነቷ፡** ኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ-መቅደሳቸው፡ ገና በሕፃንነቷ፡ ወደዚያ ልትገባ፥ በዚያም ልትኖር ስለቻለች፡ ለዚህች፡ አንዲትና አማናዊት ለኾነችበት ታቦተ ጽዮንነቷ፡ ትልቅ ማስረጃና ማረጋገጫ ሊኾን በቅቷል።

አዎን! ታቦተ ጽዮን፡ በዚህ መልኩ ነበር፡ በእናቲቱ፡ በድንግል ማርያምና በወልደ እግዚአብሔር ልጇ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡ ከማረፊያዋ አኵስም ተነሥታ፡ የቀዳማውያቱ አርአያዎቿን፡ የኢትዮጵያውያቱን የሓመረ ኖኅንና የንግሥተ ዓዜብን ፈለግ በመከተል፡ ቀድሞ፡ ከኢየሩሳሌም ተነሥታ፡ ወደኢትዮጵያ በመጣችበት፡ በዚያው መንገድ፡ በቅድስት ሓና የትስብእት መርከብ ማሕፀን ውስጥ ኾና፡ "ቀይ ባሕር" በተባለው፡ በባሕረ ነጋሽ በኵል አቋርጣ፡ ወደኢየሩሳሌም የተመለሰችው።

ነገር ግን፡ አይሁድ፡ ይህን ኹሉ መለኮታዊ ቸርነት ዐውቀው፡ እንኳንስ፡ በመልካም ሊቀበሏት ይቅርና፡ በተለመደ ቅንዓታቸውና ተቃውሟቸው፡ ምን ዓይነት ወሮታን እንደመለሱ መመልከት ነው፤ ይኸውም፡ እነዚህኑ እናትና ልጅ፡ በማሳደድና በማንከራተት፥ በመጨረሻም፡ ልጇን፡ የሾህ አክሊልን በማቀዳጀት፡ በደም የታለለ ራሱን፥ ፊቱንና አንገቱን የተሸከመውን፥ እንዲሁም፡ የፊጥኝ አሥረው፡ በግርፋት የተለተሉትን፡ ያን፡ መላ ሥጋዊ አካሉን፡ ዕርቃኑን፡ በመስቀል ላይ ዘርግተውና ወጥረው፡ እጆቹንና እግሮቹን በመቸንከር፥ ጎኑንም በጦር በመውጋት፡ አሠቃይተው ለገደሉት፥ አዎን! "የአባቶቻችን፡ የአብርሃም፥ የይስሓቅና የያዕቆብ አምላክ!" ለሚሉት፡ ለዚያ እግዚአብሔር፡ ያላቸውንና የቀራቸውን፡ የመጨረሻ መራር ጥላቻ፡ በገሃድ ገልጸው ማሳየታቸው ነው። (ማቴ. ፳፯፥ ፳፯-፶፩። ዮሓ. ፲፱፥ ፩-፴፯።)

እናትና ልጅ፡ እንዲህ፡ ሞትንና ሙስና መቃብርን (በመቃብር መበስበስን) በትንሣኤያቸው፡ ካጠፉልንና ካስወገዱልን በኋላ፡ ዛሬና ለዘለዓለም በምንኖርባት፥ ህልውናዋም፡ በንጉሧ አንደበት፡ ***"...መንግሥተ ዘአስተዳለወ፡...እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም!"***

*ማለትም፡ "...ዓለም ሳይፈጠር፡ ያዘጋጀላችሁን መንግሥት"፥*

*በዜጐቿም አንደበት፡ "እምቅድመ ዓለም፡ ህልዎትኪ!"፡*

*ማለትም፡ "ህልውናሽ (አኗኗርሽ)፡ ከዓለሙ በፊት ነው!" የተባለላት፡* <u>*ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው*</u> <u>**ድንግል ማርያም**፡</u> በሰማያትና በምድር ሞልታና ሰፍና ባለችው ቤተ መቅደስ ውስጥ፡ ***"...ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር፡ እንተ ውስተ መቅደሱ!"***

*ማለትም፡ በሴት አንቀጽ፡ "በሰማያት ያለችው፡ 'የእግዚአብሔር፡ የሕጉ ታቦት' ታየች! ተገለጸች!" ተብላ፡ እነሆ! ፍጥረቶቿን፡ በሕያውነት ታስተዳድራለች።*

*(ማቴ. ፳፭፥ ፴፬። መጽሓፈ ሰዓታት፤ ስብሓተ ፍቍር ዘእግዝእትነ ማርያም፡ ዘደረሰ ገዳማዊ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ። ራእ. ፲፩፥ ፲፭።)*

\+ \+ \+